Abyss. J. Cul. Ind. Kn. Vol. 1, No. 1, 2022, 41-49
DOI: https://doi.org/ 10.20372/ajcik.2022.1.1.694
Publisher: Wollo University, Dessie, Ethiopia

**Abyssinia Journal of Culture and Indigenous Knowledge**

# ቃል ግጥሞች እንደ ግብረገብ ማሔሻ ዘዴ በደቡብ አቸፈር ወረዳ አብችክሊ አካባቢ

**ደሳለኝ ሥዩም*[1]**

1. በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት ዲግሪ ተማሪ

**አህጽሮተጥናት**

*የዚህ ጥናት ዓላማ ከአብችክሊ ዙሪያ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን የግብረ ገበ ማሔሻነት ሚና መፈተሽ ነው፡፡ ግጥሞቹ ሊሰበሰቡ የቻሉት በመስክ ምልከታ እና ድምጽ ቀረጻ ስነዳ ነው፡፡ የጥናቱ ዘዴ ዓይታዊ ሲሆን ለመፈተቻነት የተመረጠው ንድፈ ሐሳብም መዋቅራዊ ባለሚናነት (Structural Functionalism) ነው፡፡ በጥናቱ ማረጋገጥ እንደተቻለው ግጥሞቹ የማኅበረሰቡ አባላት ከማንነታቸው፣ ከምግባራው እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃቸው ላይ በማነጣጠር እርስ በእርስ የሚተቻቹበት መሆኑን እና የቃል ግጥሞች ሚና ከግብረ ገብ ሒስ አንጻር አዎንታዊ መሆኑ ነው፡፡*

**ቁልፍ ቃላት፡-** ቃል ግጥም፣ ማህበራዊ ፋይዳ፣ ግብረ ገብ፣ ማሔሻ

## መግቢያ

ቃል ግጥም ሳይጻፍ የተፈጠረ፣ ሳይጻፍ ትውልድን እና ድንበር የሚሻገር የማኅበረሰብ ኪን ነው፡፡ የፈጠራው ዋነኛ መነሻ የሚሆነው ክስተት ወይም ሁነት ነው፡፡ Finnegan እንደሚሉት ቃል ግጥም የማኅበረሰቡ የጋራ የሆነ ነው፤ የጋራ ስለሆንም የጋራ ተቀባይት ያለው ተፈጥሮ አለው፤ አያፈነግጠም፣ አይደነግጥም፡፡ ባለማፈንገጡ ከማኅበረሰቡ እውነታዎች ውጭ አይዘልም፣ ባለመደንገጡ የማኅበረሰቡ የሆኑ እውነታዎችን ችላ ብሎ አያልፍም፡፡ Oral poetry is not an odd or aberrant phenomenon in human culture, nor a fossilised survival from the far past, destined to wither away with increasing modernisation. (1977:4) ታሪክን ያስቀምጣል፣ ባህልን ያስቀጥላል፣ ትውልድን ከትውልድ ያጋምዳል፡፡ ቃል ግጥም የማኅበረሰብ ሀብት ነው፤ ስለዚህም የትም ተመስርቶ እስከየትም ሊጓዝ ይችላል፤ ቃል ግጥም የጉዳይ ገደብ የለበትም፣ ስለዚህም የፈለገውን ነገር ሊያነሣ ይችላል፤ ነገር ግን ቃል ግጥም ሚና አለው፡፡

> Oral poetry played an important role in the social life of a people or community, expressing its collective world view, its system of religion, its moral values, its history and its dreams for the future (Cuddon (2013: 496) .

አንድ ማኅበረሰብ አባላት ይሩታል፤ እኚህ አባላቱ ባልተጻፈ - ነገር ግን በሚያግባባ ደምብ ይኖራሉ፤ ያልተጻፈ - ነገር ግን የሚያግባባ ደምብ የሚያኖራቸው ከሆነ ደግሞ ይህ ለመሆኑ አንዳች ገፊ ምክንያት ያስፈልጋል፤ ገፊ ምክንያት ሊሆኑ ከሚችሉ ደግሞ የቃል ግጥም የማኅበረሰቡን አባላት በማሔስ የሚኖረው ሚና አንዱ ሆኖ ይመጣል፡፡ አባቶች የሰሩትን ደምብ ለልጆች ያስተላልፋል፤ ልጆች የኖሩን ኑሮ ለልጅ ልጅ ያሻግራል፡፡ ለማሔሻነት ሚና አለው ሲባም የማኅበረሰቡ ነዋሪ አባላት (present generation) ከቀዳሚ አባላት (past generation) ደምብ ያፈነገጡ እንዳይሆኑ መጭ አባላቱም (future generation) ከነዋሪ አባላቱ ሥሪት የወጡ እንዳይሆኑ የመገምገምን፣ የማረምን ብሎም የማሞግስን ሥራ ይሰራል ማለት ነው፡፡ Finnegan እንዲህ ይላሉ፡፡

> 'Oral tradition' (including what we should now call oral literature) is passed down word for word from one generation and thus reproduced verbatim from memory throughout the centuries, or alternatively, that oral literature is something that arises communally, from the people or the 'folk' as a whole, so that there can be no question of individual authorship or originality. (Finnegan, 1970: 14)

ግለሰባዊ ፍላጎቶች ወይም ማፈንገጦች ለሰፊው ማኅበረሰብ ጥቅምና ደህንነት ሲባል ወደ ውስጥ ዋጥ ሲደረጉ ማኅበረሰባዊ የሆኑ የጋራ እሴቶች ይጎለብታሉ፤ የእኚህ እሴቶች ዋነኛ ተግባር ደግሞ ማኅበሰረቡን ሰላማዊ፣ የተረጋጋ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ እና እያደር በአዎንታዊነት የሚያድጉ ምግባሮች ባለቤት ማድረግ ይሆናል፡፡ የዚህ ዋነኛ ዘዴው ደግሞ ማኅበራዊ ቁጥጥር (social control)

* Corresponding Author’s Email: desephilo@gmail.com

ሲሆን ይሄ ማህበራዊ ቁጥጥር መደበኛ (formal) እና ኢ-መደበኛ (informal) መንገዶች ይኖሩታል፡፡ ኢ-መደበኛ የሆነውን ማኅበራዊ ቁጥጥር ሚና ከሚወጡ ማኅበረሰባዊ ኪኖች መኻል ቃል ግጥም አንዱ ነው፡፡

የአንድ ማኅበረሰብ አባላት በማኅበራቸው ውስጥ ልዩ ልዩ ተሳትፎዎችን ያደርጋሉ፡፡ የስራ ተሳትፎ፣ የባህላዊ ድርጊያዎች ተሳትፎ፣ የልማዳዊና ዕምነታዊ ድርጊያዎች ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ እንደ እንቆቅልሽ፣ እንካስላንታያ፣ ተረት፣ ታሪክ ነገራ፣ ሙሾ፣ ስለምን፣ ጭፈራ፣ ዝላይ ውሃ ዋና እና ሌሎች ነገሮች ማኅበራዊ መገናኛዎች ሆነው ያገለግላሉ፡፡

የዚህ ጥናቱ ዋና ዓላማ ቃል ግጥሞች በተመረጠው አካባቢ ለማኅበረሰቡ የግብረ ገብ ማሔሻ ዘዴ በመሆን ያላቸውን ሚና መፈተሽና መዘርዘር (description) ማሰናዳት ነው፡፡ ጥናቱ የተደረገባቸው ቃል ግጥሞች የተሰበሰቡት በምእራብ ጎጃም ዞን ደቡብ አቸፈር ወረዳ አብችክሊ አካባቢ ነው፡፡ ቦታው የተመረጠበት አመክዮ (site selection rational) የጥናቱ አጥኚ በቤተሰብ ጉዳይ ወደ ሥፍራው ደጋግሞ መመላለሱ፣ የአካባቢውን ዙሪያ ገብ የሚያውቅ በመሆኑ፣ ቦታው ቃል ግጥሞች በዕለት ከዕለት ግንኙነት ሁሉ አገልግሎት ላይ የሚውልበት መሆኑ እና አጥኚው በአካባቢው የሚነገሩ ቃል ግጥሞችን ግልብና ክንብንብ (overt and covert) ፍችዎች ለመረዳት የሚያስችል የአካባቢው ዘዬ አዋቂ መሆኑ ነው፡፡ ግጥሞች የተሰበሰቡት የአካባቢው ማኅበረሰብ አብዝቶ የሚዘክራውን (የሚያከብራቸውን) ታቦታት በዓላት ምክንያት በማድረግ በሚዘጋጁ ድግሶች ላይ በመገኘት ነው፡፡

ግጥሞችን ለማሰባሰብ የተመረጠው የካቲት ማርያም ወይም የካቲት 21 ነው፡፡ ይሄ ወር እንደ ታህሳስ ገብርኤል፣ ገና፣ ጥምቀት፣ ቃና ዘገሊላ እና አስተርዕዮ፣ የተሰኙ ታላቅ በዓላት ተከብረው ካለፉ በኋላ ድግስ በሚጠፋበት ወቅት ላይ የሚመጣ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የካቲት ከሞላ ጎደል ገበሬው ስራው ቀለል የሚልለት ወቅት በመሆኑ ዘና ብሎ ለመጫዎትና እንዲህ ያውን አፋዊ ግጥም የሚያዘንብበት ጊዜ መሆኑ ከምልከታ ማረጋገጥ በመቻሉ ነው፡፡

ግጥሞች በሞባይል ስልክ የድምጽ ቀረጻ በማድረግ ነው የተሰበሰቡት፡፡ የድምጽ ቀረጻው የተካሄደው በድብቅ ሲሆን ይህም የሆነው ተሳታፊዎቹ ቀረጻው በሚፈጥርባቸው ተጽእኖ የተነሣ የስሜት ከንቱነት (artificialness) እንዳይታይባቸው ነው፡፡ በሌላ በኩል የድምጽ ቀረጻውን ተሳታፊዎቹ በማያውቁበት መንገድ ማከናወኑ የግለሰቦችንም ይሁን የማኅበረሰቡን ምሥጢር የማያባክን፣ የግለሰብን ይሁን የማኅበረሰብን ማንነት ያማያንኳስስ፣ የማይፈርጅ እና ለማጥቃት የተነሣ ጥናት ባለመሆኑ ያለተሳታፊዎች እውቅና ግጥሞችን በድምጽ ሰንዶ መያዙን አጥኚው አምኖበታል፡፡

ጥናቱ ዓይታዊ ጥናት ነው፡፡ ከዓይታዊም ገላጭ አይነታዊ፡፡ የተሰበሰቡ ግጥሞች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ሚና (Function) ከ መዋቅራዊ ባለሚነናነት (Structural Functionalism) ሥነ ማኅበረሰባዊ ንድፈ ሐሳብ በመነሣት ትንታኔ ይደረግባቸዋል፡፡ የቃል ግጥሞቹ ሚና ምን እና እንዴት እንደሆነ በዝርዝር ይበይነበታል፤ ጥናቱ፡፡ ይህ ጥናት ከዚህ መግቢያ በኋላ ሁለት ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው ንድፈ ሐሳቦችን የምንመለከትበት ይሆንና ተከታዩ ደግሞ የትንታኔ ክፍል ይሆናል፡፡

## ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት

በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋለው ንድፈ ሐሳብ 'መዋቅራዊ ባለሚናነት' (Structural Functionalism) ወይም አጠር ተደርጎ ሲገለጽ 'ባለሚናነት' (Functionalism) ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ንድፈ ሐሳቡ ምን እንደሆነ በአጭሩ እንመለከት፡፡

የዚህ ንደፈ ሐሳብ ብሉይ አቀንቃኞች ሳይንሱን ከሰው ልጅ ሥነ-ሕይወታዊ መዋቅር ነበር የተዋሱት፡፡ እንደ Auguste Comte ለመሰሉ የዘመኑ አሳቢያን ሥነ ሕይወት ከሌሎች ሳይንሶች በተሻለ ለማኅበራዊ ሳይንስ ቅርበት አለው፡፡ ይሄንን የComte እና የዘመነኞቹን ዕይታ የእንግሊዙ Anthony Giddens እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡፡

> Biology has been taken to provide a guide to conceptualizing the structure and function of social systems and to analyzing processes of evolution via mechanisms of adaption. (2005:88)

አሳቢያኑ ከሥነ ሕይወት የተዋሱት የሥነ ሕይወት የአጠናን ስልት 'ኩፋሌ ቅርጽና አገልግሎት' (Anatomy and Physiology) ነው፡፡ የሰው ሰውነት የራሱ ቅርጽ አለው፤ ይሄንን ቅርጽ እንዲይዝ ያደረጉት ልዩ ልዩ የሰው ልጅ የአካል ክፍሎች በአግባቡ ተሰድረው እርስ በእርስም ተናበው በመሥራታቸው ነው፡፡ በተጨማሪ በቅርጹ ውስጥ ያሉ አካል ክፍሎች እርስ በእርሳቸው ሳይጣረሱ ይልቁንም በመናበብ የሚሠሯቸው የየራሳቸው ሚናዎች አሏቸው፡፡

ሥነ-ሕይወት (Biology) የሰውን አካል እንዲህ አድርጎ እንደሚያጠናው ሁሉ እነ Emile Durkheim የአጠናን ስልቱን ወደ ማኅበራዊ ሳይንስ ይልቁንም ወደ 'ሥነ ሰብ'ና 'ሥነ ማህበረሰብ' (Anthropology and Sociology) ጥናቶች አምጥተውታል፡፡

በእነ Comte ፈር ቀያሽነት በኋላም በ Durkheim አቀናባሪነት ተስፋፍቶ የመጣው የባለሚናት ንድፈ

ሐሳብ አንድን ትልቅ ማኅበረሰብ ሳይሳዊ በሆነ ዘዴ ለማጥናት መግቢያ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ አንድ ሰፊ ወይም ትልቅ ማኅበረሰብ ሰላሙን፣ ቅርጹን እምነቱንና ሥርዓቱን ጠብቆ ያለመነዋወጥ እንዴት ሊኖር ይችላል? ውስጣዊ ሰላሙ፣ እና መረጋጋቱ ጊዜ የማይሽረው አለመናዋወጽ እንዲኖር ያስቻለው ጥበብ ምንነቱን ማወቅ ያስችል ዘንድ ይሄ የባለሚናነት ንድፈ ሐሳብ ብርቱ ጠቀሜታ አለው፡፡ የእነ Durkheimን ምልከታ በምሳሌ ለማዬት ያህል የሚከተለውን እንጥቀስ፡፡

ለምሳሌ የወሎ ማኅበረሰብ ወይም በሰፊው የአማራ ህዝብ ወይም በጣም በሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ሆኖ ይሄን ያህል ዘመን ሊኖር ያስቻለው ጥበብ ምንድን ነው? አልደፈር ባይነቱ፣ ሰው አክባሪነቱ፣ ሀገር ወዳድነቱ፣ ወዘተ. እንዴት ያለመነዋወጽ እዚህ ደረሰ? ለዚህ መልሱ ይላሉ እነ Durkheim እና ሌሎችም የባለሚናነት ንድፈ ሐሳብ አቀንቃኞች በእያንዳንዱ ማኅበረሰባዊ መዋቅር ውስጥ ማለትም እረኞች፣ ጠረኞች፣ እናቶች፣ በረኸኞች፣ ደጎች፣ ገበያተኞች፣ ሃይማኖተኞች፣ ህጻናት፣ ኮረዶች፣ ሽማግሎች፣ ድሆች፣ ሀብታሞች፣ ሰራተኞች፣ ካህናትና መናኒያን ወዘተ በየመዋቅራቸው ውስጥ የሚያሔዷቸው የህዝቡ እሴቶች፣ ልማዶች፣ ድርጊያዎች፣ እውቀቶች፣ እምነቶች፣ ባህሎች፣ ክህሎቶች ይሄንን መዋቅር ጠብቀውት ይኖራሉ፡፡ በሌላ አባባል እኒህ የተጠቀሱ የመዋቅሩ ክፍሎች እንደ አካል ክፍል የሚታዩ ሲሆን ተግባሮቻቸውም እንደ የሰው ልጅ አካል ክፍሎች ተግባሮች አንዱ ላንዱ የግድ አስፈላጊና አዎንታዊ ነው፡፡

ንድፈ ሐሳቡ በሥነ ሰብና በሥነ ማኅበረሰብ ጥናቶች በትልቁ አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ ይሄ ንድፈ ሐሳብ ማኅበረሰብ ልክ እንደ ሰው ልጅ ቁመና ከልዩ ልዩ አካል ክፍሎች የሚዋቀር ነው ብሎ ያስባል፡፡ ልክ የሰው ልጅ ይሄን ዓይነት ቁመና ወይም ቅርጽ እንዲኖረውና በትክክል የሰው ልጅ ተግባራትን እንዲወጣ እያንዳንዱ የአካል ክፍል የየራሱ የሆነ ገንቢ ሚና አለው፤ ማኅበረሰቡም አንድ ማኅበረሰብ ሆኖ ለመቆም የየራሳቸውን በጎ ሚና በሚጫዎቱ አካል ክፍሎች ይዋቀራል፡፡

እነዚህ ማኅበረሰቡን የሚፈጥሩት የመዋቅሩ አካላት (Organs) የሚታዩ ወይም የማይታዩ የሚዳሰሱ አለዚያም የማይዳሰሱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በአንድ ውቅር ማኅበረሰብ ውስጥ የሰው ልጅ ልማዶች፣ ወጎች፣ ባህሎች፣ ማኅበራዊ ተቋማት፣ ድርጊያዎች፣ ግብሮች፣ እምነቶች፣ ሰዎችና ቡድኖች፣ ቀለሞችና ቅርጾች ወዘተ. ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

በዚህ ንድፈ ሐሳብ ውስጥ ጎልቶ የወጣውን ‹አካል› (organ) የተባለውን አገላለጽ ይበልጥ ያስተዋወቀው Herbert Spencer የተባለ ሶሽዮሎጅስት ነው፡፡ (Urry 2000:23) እነዚህ አካላት (organ) ለሰውነት ጠቅላላ ጤናማነትና ምሉዕነት ብሎም ሰላማዊና የተራዘመ ሕልውና እንዲኖር ተግባሮቻቸውን ይወጣሉ፡፡

> "The effort to impute, as rigorously as possible, to each feature, custom, or practice, its effect on the functioning of a supposedly stable, cohesive system" (Bourricaud 1975: 94)

ገበሬው ተግባሩ እርሻ እያረሰ፣ ንብ እያነበ አለዚያም አሳ አስግሮ ወይም ከብት አርብቶ ለራሱና ለሌሎችም መኖር ነው፡፡ የገበሬው ተግባሮች ማኅበሰረቡ እንዳይራብ፣ ችጋር ገብቶ ሰው እርስ በእርሱ እንዳይበላላ ያስችላል፡፡

ካህኑ ይቀድሳል፣ ይጸልያል፣ ይመክራል፣ ጾምን ጸሎትን እርቅን ሽምግልናን ያስተባብራል፣ ይሄን በማድረግም ለራሱና ለማኅበሰረቡ ይኖራል፡፡ የሃይማኖት አባት እንዲህ ያለውን ተግባሩን በማከናወኑ ማኅበሰረቡ እና አባሎቹ ፈሪሀ እግዚአብሄር ያላቸው፣ ከፍ ያለ የሞራል ልዕልና ያላቸው ሰው አክባሪዎች፣ የሰው ሀቅ የማይፈልጉ ተመስግነውና ተወደው ለመኖር የሚፈልጉ በመካከላቸው ፍቅር ያላቸው ወዘተ. ሆነው በጋራ መኖር ይችላሉ፡፡

ከላይ የተቀመጡት ሁለት ምሳሌዎች የማኅበሰረቡን ክፍሎች (Organs) የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ልዩ ልዩ የማኅበረሰብ አደረጃጀቶች አሉ፤ በሙያ፣ በእድሜ፣ በአየር ንብረት በምግባር፣ በሃይማኖት ምልከታ፣ በጾታ ወዘተ ምደባዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በእነዚህ መደቦች ሆነው የሚያከውኗቸው ብዙ ተግባራት አሉ፡፡ ከእነዚህ ተግባራት ደግሞ ልማዳዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ወይም ባህላዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ተግባራቱ ታያ ለየብቻ የሚቆሙ ሳይሆኑ አንዱ ባንዱ የሚደጋገፉ ናቸው፡፡

ሰው ውሃ ውስጥ ገብቶ ሲዋኝ ከሚያገኘው የተዝናኖት ስሜት ባለፈ በአእምሮና በአካላዊ ጤናው ላይም አዎንታዊ እሴት ይጨምራል፡፡ ከዚህም አልፎ ዋና መቻል የጀግንነት፣ የጠረኝነት፣ የደስተኝነት፣ የደፋርነት መገለጫ ሆኖ የሚታይባቸው አካባቢዎች አሉ፡፡ ስለዚህም ዋና ከአንድ ተራ እንቅስቃሴነት ባለፈ ዘርፈ ብዙ የሆነ ሚና ይኖረዋል፤ ይሄ ሚናው ከግለሰብ ጀምሮ እስከማኅበረሰቡ ስብስብ ድረስ እንደሀረግ የተያያዘ ሚና ነው፡፡ የባለሚናነት ንድፈ ሐሳብ ምሁራን የሚሉትም ይሄንኑ ነው፤ በማህበሰብ ውስጥ ያለ ማንኛውም አካል የሚያከናውነው ተግባር የማኅበሰረቡን ትስስሮሽ የሚያጠነክር ማህበረሰብን እንደአንድ መዋቅር ጤናማነቱን ጠብቆ ለመጓዝ የሚያስችል ነው፡፡ ለዚህም ነው የአሜሪካው ሶሽሎጅስት Talcott Parsons የሚከተለውን የሚለው

> The social system is made up of the actions of individuals. The interaction between two individuals faced with a variety of choices about how they might act, choices that are influenced and constrained by a number of physical and social factors. (Parsons & Shills 1976:190)

ማኅበራዊ መዋቅር ወይም ማኅበረሰብ የምንለው አካል በግለሰቦችና በግለሰቦች ተግባሮች የተገነባ ነው፡፡ ነገር ግን ግለሰቦች በምርጫቸው ወይም በውሳኔአቸው አንዱ ካንዱ ሊለዩ የሚችሉበት አጋጣሚው ብዙ ነው፡፡ ነገር ግን የግለሰቦች ፍላጎቶችና የውሳኔ ምርጫዎች የጭቅጭቅ እና የጥላቻ መንስኤዎች እንዳይሆኑ የሚያደርጉ ማህበራዊና አካላዊ ተጽእኖዎች በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ይኖራሉ፡፡

እንዲህ ከሆነ እያዳንዱ ግለሰብ የግል ምርጫውን ብቻ ከማስቀደም ይልቅ የማኅበሰረቡን መዋቅር የሚያስጠብቅ ተግባርና ምግባር ይጠበቅበታል፡፡ ይሄንን ያላደረገ እንደሆነ በተቃራኒው ከማኅበሰረቡ የመገለል፣ የመወቀስ፣ የመንቋሸሽ እንዲያም ሲል እንደወንጀለኛ የመታዬት እጣ ፈንታ ሊደርስበት ይችላል፡፡

በመዋቅራዊ ባለሚናነት ንድፈ ሐሳብ መሠረት ማኅበረሰብ ውስጥ የሚከወኑ የግለሰብ ትግባራት ምንጊዜም ሁለት ውጤቶችን ሊያስከትሉ ይላሉ፡፡ ሐሳቡን የምንዋሰው ከ Robert Merton ነው፡፡ Merton የአንድ ግለሰብ ድርጊያዎች በሁለት መንገዶች ሊታዩ እንደሚገባ ይጠቁማል፣ ለአንድ ነገር ብቻ፣ ግለሰቡና ድርጊያው በማኅበሰረቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና ለመገምገም፡፡

ግለሰቡ ያደረገው ድርጊያ ሁለት ውጤቶች ይኖሩታል፣ እንደ Merton እይታ፡፡ የመጀመሪያው የታቀደለት፣ የታሰበበትና እንዲሆን የሚጠበቀው የድርጊያው ቀጥተኛ ውጤት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ያልታሰበ፣ በውስጠ ታዋቂ የተፈጠረ፣ ያልታቀደ ውጤት ነው፡፡ የመጀመሪያውና ቀጥተኛው manifest function የሚባል ሲሆን ሁለተኛውና ኢቀጥተኛ ውጤት Latent function ይባላል (Merton, 1957፡51)፡፡

እንደ Merton አስተውሎት ከሆነ አንድ ሰው ወደ ትምህርት ቤት የሚገባው ትምህርት ለመቅሰም በሚል ዓላማ ነው፡፡ ለምሳሌ ሒሳብ ወይም አማርኛ የተባለ ትምህርትን ለመማር ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳል፡፡ የዚህ ሰው ተግባር መማር ነው፤ በዚህ መሠረት ቀጥተኛ ተግባሩ እነዚህን ትምህርቶች መማር ነው፡፡ ነገር ግን ያልታሰበበት ተግባሩ ደግሞ አልባሌ የጸጉር አያያዝ ወይም አነጋገር አለዚያም እንደሲጋራና መሰል ልማዶችን መልመድ ሊሆን ይችላል (Merton, 1957፡51)፡፡

አንድ ሰው በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሲኖር ዕለት በዕለት ልዩ ልዩ ተግባሮችን ያከናውናል፣ ቃሎችን ይናገራል፣ ዜማዎችን ያዜማል፣ ጸሎቶችን ይጸልያል፣ ሌሎችንም ተግባሮች ያከናውናል፡፡ በ Merton እይታ ይሄንን ሁሉ ተግባር አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አድርጎ ብቻ ከመውሰድ ይልቅ የታሰበበት ተግባርና ሳይሳተሰብ የተደረገውን ተግባር ለይቶ ማዬት መልካም ነው ማለት ነው፡፡

ይሄንን ክፍል ለማጠቃለል የመዋቅራዊ ባለሚናነትን ሁነኛ መከራከሪያ እናስቀምጥ፡፡ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ አባላት በሙሉ ያለ ጾጰ፣ ኢኮኖሚ፣ ቋንቋ፣ ቀለም ወይም ሌላ መስፈርት ልዩነት ለማኅበረሰቡ አስፈላጊ ናቸው፡፡ አበላቱ ብቻ ሳይሆኑ ኣባለቱ የሚያደርጓቸው እንቅስሴዎች፣ የሚያዋጧቸው እውቀቶች፣ የሚተገብሯቸው ተግባራት፣ የሚናገሯቸው ንግግሮች ወዘተ. ማኅበረሰቡ ራሱን ጠብቆ እንዲዘልቅ የሚያችሉ አዎንታዊ አስተዋጽኦዎች ናቸው፡፡

## የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ክፍል የተሰበሰቡ የቃል ግጥሞች ይተነተናሉ፡፡ ለትንታኔ ያመች ዘንድ ግጥሞቹ በሶስት መደቦች ተከፍለው ተቀምጠዋል፡፡ የመጀመሪያው ማንነት (Identity) ላይ ያተኮሩ ግጥሞች መደብ ነው፡፡ ሁለተኛው ምግባር (Ethics) ላይ ሶስተኛው ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች (Economic Status) ላይ የሚያጠነጥኑ ግጥሞች ይታያሉ፡፡ ሦስቱም መደቦች በተልቁ ምስል ግብረ ገብ (Morality) ጋር የሚገናኙ ናቸው፡፡

የቃል ግጥቹ በሰተሰበሰቡበት አካባቢ የገጠር ቀበሌዎች መደበኛ ከሆኑት ዓመታዊ ወይም የንግስ በዓላት ባለፈ እያንዳንዱ አባዎራ ቢያስ አንድ ወርሃዊ የማኅበር ዝክርን ይሳተፋል፡፡ ለምሳሌ የገብርኤል ማኅበር ጠጭ ከሆነ በየወሩ ተረኛ የሆነው ዘካሪ ቤት ትልቅ ድግስ አለ፡፡ የማኅበሩ አባላት በበረከቱ ቁጥር ከሶስት አለዚያም ከአራት ዓመት አንዴ ነው በአንድ ግለሰብ ቤት ሊደርስ የሚችለው፤ ይሄ ማለት ተረኛው ገበሬ ግዙፍና ሰፊ ድግስ ማዘጋጀት አለበት ማለት ነው፡፡ የዚህ ዓይነት የማኅበር ድግሶች ልዩ ባሕርያቸው ከዋናው ድግስ በፊትና በኋላ ልዩ ልዩ ሥርዓቶች ያሏቸው መሆኑ ነው፡፡ ‹‹ድፍድፍ መቅመስ››፣ ‹‹ጸበል መቅመስ›› ‹‹ቅራሪ መጠጣት››፣ ‹‹ሲጫዎቱ ማምሸት›› የሚሉ ሂደቶች አሉበት፡፡ እነዚህ ሥርዓቶች ከዋናው ዝክር ዋዜማ ጀምሮ ድኅረ ድግስ ሁለት እና ሦስት ቀናትን ሊያስከትል የሚችል ነው፡፡

ጠቅላላ ምልከታው ሶስት ቀናትን ፈጅቷል፤ ከየካቲት 20-22 /2010 ዓ.ም ሶስት ምሽቶችን በዚያ የድግስ ስፍራ እየተገኘ የዚህ ጥናት አቅራቢ የመዘገባቸው የስለምን ግጥሞች ለአካባቢው ማኅበረሰብ የሚኖራቸው ግብረገባዊ ፋይዳ ይተነተናል፡፡

### ሀ.ማንነት ላይ ያተኮሩ ግጥሞች

በዚህ መደብ የተቀመጡ ቃል ግጥሞች አጥኚው በድግሶቹ ላይ በተገኘባቸው ጊዜዎች የሰበሰባቸው ናቸው፡፡ ግጥሞቹ በግለሰቦች አለባበስ፣ አነጋገር፣ አኗኗር፣ ወግ፣ ልማድ፣ ሃይማኖታዊ ድርጊያዎች ወዘተ. ላይ የሚያተኩሩና በዋናነት እንዲህ ዓይነት ግበረ ገባዊ ተሳትፎዎች ውስጥ ስንፍና የታዩባቸውን ግለሰቦች ለመሸንቆጥ የተገጠሙ ናቸው፡፡ ሁነቱ እንዲህ ነው፡፡ የካቲት 22/2010 ዓ.ም በድግሱ ቤት ውስጥ የማርያም ማኅበር ሶስተኛው የድግስ ቀን እየተካሄደ ነው፡፡

ዕለቱ የማኅበሩ አባላትና ጎረቤቶች ‹ቅራሪ ጠጡ› ተብለው የሚጠሩበት ነው፡፡ ለዚህ እለት ከጠላው ባለፈ የገብስ ቆሎ በሽምብራ ይቀርባል፡፡ የእለቱ ዋነኛ አጀንዳ የሚሆነው ለቀጣይ ወር ማኅበር የሚያወጣውን ሰው መርጦ የተረኝነት ዋንጫውን መስጠት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ መሳቅ መጫዎት ነው የማኅበሩ አባላት ተሳትፎ፡፡

በዚህ መሃል ከቀንድ የተሰራ ዋንጫውን ተረከዝ ይዞ (በአካባቢው ልማድ መሠረት ማህበርተኞች ጠላ የሚጠጡበትን እቃ ከዬቤታቸው ነው ይዘው የሚመጡት) ጠላውን የሚያጣጥም ባለ ነጭ ኩታ ማህበርተኛ ዳሱ በር አካባቢ ጎጃም አዘነውን ተከናንቦ ተረከዝ በሌለው የሸክላ ዋንጫ (አፍሻት) ጠላውን የሚጠጣን አንድ ሰው ገርመም እያደረገ

ትልቁን ተራራ ትንሹ ጋርዶታል

ዋንጫ ማያምርበት አፍሻት ይጎትታል

ሲል ይገጥምበታል፡፡ ‹‹ዋንጫ›› ከቀንድ የሚሠራ የተዋበ እና ክብር ያለው መጠጫ ነው፡፡ ‹‹አፍሻት›› የሚባለው መጠጫ ከሸክላ የሚሠራ ተረከዝ የሌለው እንደነገሩ ተሠርቶ ላልፎ ሂያጅ ጠላ የሚሠጥበት እና የረባ ክር የሌው መጠጫ ነው፡፡ በሌላ በኩል ግጥሙን ያለው ሰው የለበሰው ነጭ ኩታ ነው፡፡ ነጭ ኩ የክብር መገለጫ ከመሆኑም በላይ በአካባው ለአደባባይ የሚለበስ ልዩ ልብስ ነው፡፡ ልብስነቱ የለባሹን ማንነት የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን የባለቤቱን ፈታይነት የሚመሰክር ህያው ቅርስም ሆኖ ይቆጠራል፡፡ የተገጠመበት ሰው ደግሞ የለበሰው ጎጃም አዘነ ነው፤ ጎጃም አዘነ በእጅ የሚፈተል ሳይን የፋብሪካ ክርን እርስ በእርስ በመሸመን የሚገል ልብስ ነው፡፡ ይህ ልብስ በአካባቢው የተናቀ ሲልም የ ‹‹እረኞች›› ልብስ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

ማኅበርተኛው ግጥሙን ለማጣጣምና ለመመነዛዘር ጊዜ ባይወስድበትም  የዚህ ጥናት አጥኚ ግን ግጥሙ ለምን እንደተገጠመ ለማወቅ ከማኅበርተኞቹ ጥቂቱን መጠየቅ ነበረበት፡፡ የማህበርተኞቹ ምላሽ ግጥሙን አብራርቶለታል፡፡

በአካባቢው ደምብ መሰረት ከቀንድ የተሰራ ዋንጫ የተከበረ ሰው የመጠጫ እቃ ነው፡፡ ዋንጫ በቤቱ ውስጥ ያለ ሰው ደርባባ እና ወግ አዋቂ ሲሆን የተደራጀ ኑሮንም የሚኖር ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ የሸክላ መጠጫ ሆኖ ተረከዝ የሌለው ወይም በአካባቢው አጠራር ‹‹አፍሻት››ን እንደመጠጫ የሚጠቀም ግድ የለሽ ብድሩን የማይመልስ፣ በጥቅሉ ከጉብሎች ተለይቶ የማይታይ ነው፡፡ ቤቱም እንደነገሩ ኑሮም ከእጅ ወደ አፍ ነው፡፡

ገጣሚው ይሄንን ግጥም ሲገጥም ትልቁን ተራራ ትንሹ ጋርደታል ብሎ መጀመሩ ‹‹ወግ አዋቂው ወይም ባህሉን አክባሪውና የተከበረው ሰው ከአንድ ኩታራ ጋር ቁጭ ብሎ ጠጣ›› የሚለውን የቁጭት ስሜት ለመግለጽ ነው፡፡ በዚህም ሰውዬውን ወደ ቁጭት በማስገባት ታታሪ ገበሬ እንዲሆን ለመምከር ያለመ ነው፡፡

ነገር ግን ‹‹ዋንጫ›› በማኅበር ውስጥ ሌላም ፍካሬ አላት፡፡ ዋንጫ ማያምርበት አፍሻት ይጎትታል ብሎ ገጣሚው ግጥሙን ሲዘጋው መደበኛ ማኅበርተኛ ሆኖ በአካባቢው ወግ መሰረት በተራው ደግሶ ከማጠጣት ይልቅ እንደለማኝ አንገቱን ደፍቶ ተሸማቆ ቅራሪ ማንቃረር ነውር መሆኑን ለማጠየቅ ነው፡፡ የተገጠመበት ሰው እውነትም ወግ የማያውቅ መሆኑን አጥኚው ለመረዳት ችሏል፡፡ ሰውየው ግጥሙን ተረድቶ ግጥሙን በግጥም መመለስ አልቻለም፡፡ ከዚህም በላይ ምን እንደተባለ እንኳ ሊገነዘብ የቻለ አለመሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ይህን ለማወቅ የተቻለው የተገጠመበት ሰው በግጥሙ ውስጥም ተሳትፎ ባለማድረጉ ነው፡፡

አንዲት ሴት ማኅበርተኛ ከዚህ ሰው ጋር የምትኖር ሴት እንዴት ያለች ‹‹ገልቱ›› መሆኗን በሚከተለው ግጥም ጠቆመች፡፡ (የዚህ ጥናት አቅራቢ ይሄን ግጥም አስቀድሞ ያውቀው ስለነበር የሴትዮዋ ፈጠራ ነው ብሎ አያምንም)

ወንዱ ተሰብስቦ ሴቱን ቢከሰው

አዘነ ጎጃሜ ተውሶ አስፈታው

በአካባቢው ልማድ ኩታ ነገር ጫንቃ ላይ ደረብ ሳይደረግ ሀዘንም ይሁን ደስታን መድረስ ነውር ነው፡፡ እንዲህ ባለ ድግስ ላይ ደግሞ ነጭ ኩታ ለብሶ መገኘት ወግ ነው፡፡ ይሁንና ያ ባለአፍሻት ግለሰብ ጎጃም አዘነ ለብሶ ነበር በስፍራው የተገኘው፤ ይሄ ማለት ሚስቱ ፈታይ አይደለችም ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ነው ወንዶች ሰብሰብ

ብለው ሚስቶቻችን ‹‹አልፈትል አሉ›› ብለው ቢከሱም ዘመን አመጣሹ ጎጃም አዘነ ማኅበርም ላይ ተልብሷልና ለሴቶቹ እንደዋስ ሆነ የሚለው ግጥም የተገጠመው፡፡ በዚህ ግጥም በተወቃሹ ማንነት ላይ ያተኮሩ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል፤ ግጥሞቹ ግበረ ገባዊ ሒስ ለማድረግ የቀረቡ ናቸው፡፡ ግጥሙ የተገጠመበት ሰው ወዲያውኑ ሊረዳቸው ከቻለ አለዚያም በቀጣይ ሕይወቱ ይሄ ግጥም በእሱ ላይ የተገጠመ መሆኑን አውቆ የተነቀፈበትን ጎኑን ሊያስተካክል ይችላል፡፡ በዚህም ግጥሞቹ እንደ ግብረ ገብ ማሔሻ ዘዴ ውለዋል ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

**ለ.ምግባር ላይ ያተኮሩ ግጥሞች**

የካቲት 21/2010 በድግሱ *ሥፍራ* የሞቀ የቃል ግጥም ውርርድ ነበር፡፡ ይህ እለት ዋነኛው ድግስ የነበረበት ነው፡፡ ትናንት ድፍድፍ ቅመሱ የተባለለት ዋናው ጠላ ዛሬ ቀረበ ማለት ነው፡፡ በአካበቢው ነዋሪ አገላለጽ ‹‹*ጠላ በጋን ተሾሟል፤ ጭልፋ የሚሰብር ሽሮ ተሰርቷል፣ እንጀራው የሚናድ መስሎ ተደርድሯል*›› የእለቱ ቃል ግጥም ነገራ የተጀመረው በፍቅር ግጥም ነበር እንዲህ ተብሎ

እመቤቴ እያልኩኝ ስሟን ሳነሳት

ለኩሳብኝ ሄደች በገላዬ እሳት

አጥኚው ይሄን ግጥም እንደሰማ ያደረገው የመጀመሪያ እርምጃ በዚያ ማኅበር ውስጥ ‹እመቤት› የምትባል ሴት ትኖር እንደሆነ መጠየቅ ነበር፡፡ ማኅበርተኞቹም አረጋገጡ፣ በዚያ ማኅበር ውስጥ ከዚህ ቀደም ከባሏ ጋር አሁን ደግሞ ባሏ ስላረፈ ብቻዋን ማኅበር የምትጠጣ እመቤት የተባለች ሴት መኖሯ ተነገረው፡፡ ግጥሙን የገጠመው ደግሞ ከሚስቱ ተፋትቶ ማኅበር የሚጠጣ ሰው ነው፤ ነገር ግን ሚስቱም ማኅበርተኛ ሆና በዚያ ስፍራ የነበረች ናት፡፡ ግጥሙ የተፋታት ሚስቱን ለማበሳጨትም የታሰበ ይመስላል፡፡ እመቤት ለነገር የቸኮለች መሆኗን በሚያሳብቅ ሁኔታ የሚከተለውን ገጠመች

አመመኝ ብላቸው ታከሚ ይሉኛል

*መዳኒቴንማ የት ያገኙልኛል*

*መዳህኒቴ አንተ ነህ ነገር ግን ሰው አላወቀልኝም* ነው የዚህ ግጥም ፍቾው፡፡ በሁለቱም ሰዎች ዘንድ የሚታየው ነገር የእወቁልኝ ይመስላል፡፡ ሰውየው እወቁልኙን ቀጠለ

እመቤት እያሉሽ እናትና አባትሽ

እኔም ሰገድኩልሽ ሳሳሁ እያየሁሽ

ይሄ ብሽሽቅ ነው፡፡ ሰውየው እና ሴትዮዋ የተፋታችውን ሴት ለማብሸቅ አቅደውበት የገቡበት በሚመስል ሁኔታ ነው ግጥሞቹን የተካኳቸው፡፡ ነገር ግን የሌላ ማኅበርተኛ ድምጽ ተሰማ፡፡ ነገሩ አስተዛዛቢ መሆኑን በፊታቸውም የሚገልጹ ማኅበርተኛ በአካባቢው ደምብ መሰረት የላይኛውን መስመር ሁለት ጊዜ ተናግረው አድማጮቹ ትኩረት እንዳደረጉ ሲያዉቁ ቤት መድፊያውን ከረቸሙት

እኔ እንደሰማሁት በእኔ ይቅር እንጅ

ለሰሚው ይገርማል እንኳን ለፈራጅ

በጥናቱ ለመለዬት እንደተቻለው በአካባቢው ማኅበርተኛ ሆኖ የሚጠጣ እረስ በእርስ እንደስጋ ዘመድ ነው፤ በደስታው በሀዘኑ ፈጥኖ የሚደርስ ነው፡፡ ከትናንት ዛሬ ባሏ ሞተ ብሎ የራሱን ሚስት ፈትቶ ከማኅበርተኛው ጋር ፍቅር ውስጥ የገባውን ሰው መውቀሳቸው ነው፡፡ ይሄ ነውር በኋላ ለሽምግልና ግራ ነው፣ የሠራችሁትም ነውር ነው፣ ተው በአደባባይ አትባልጉ፣ ወዲህ የፈታሃት ባለቤትህን እዚሁ ቁጭ አድርገህ ወዲያ ደግሞ በፊት አብሮህ ማህበር ይጠጣ የነበረ ባልንጀራህ ሚስት ወሽመህ እንዴት ያለ ኑሮ ልትኖር ነው፣ ተው ረጋ በል ነው የግጥሙ ሐሳብ፡፡ ምግባር ጎድሎሃል ሞራል ጎድሎሃል ተሳስተሃል፣ ለስህተትህ ተጸጸት ነው፡፡ ወዲያውም ባልና ሚስት ቢጣላ ቢፋታ መልሶ በሽማግሌ መታረቅ ይመጣ ይሆናልና በኋላ ማጣፊያው እንዳያጥርህ ነው የሰውየው ግጥም፡፡ ጥቂት ጊዜ ጸጥ ብሎ የቆዬው የቃል ግጥም ውርርድ ከባሏ በተፋታችው ሴት ግጥም መልሶ ተቀሰቀሰ፡፡

ሰው ሁሉ በሰው ስም ይማል ይገዘት

እኔ በማተቤ ዘወትር ልሙት

መልሱ ከእሷ ቀድመው ለገጠሙት ለሶስቱም ሰዎች የታሰበበት ነው፡፡ የመጀመሪያው ከዚህ ቀደም የነበረው ባሏ ወስላታ የነበረ በመሆኑ በመፋታቷ እንደማይጸጽታት ነው የተናገረችው፡፡ ቀጥሎም ባሏ ያረፈባትም ብትሆን ዛሬ አዲስ ስለሆነች በዚህ ሰው ልትመካ ብትሞክርም እንኳ የማታ የማታ ምንም ማስተማመኛ እንደሌላት ነው፡፡ ሶስተኛው ሐሳብ ለሽማግሌው የተነገረ ነው፣ እኔ ወትሮም ቢሆን በአምላኬ እንጅ በሰው እምነት አልነበረኝም፣ ለማተቤም እሞታለሁ እንጅ ሰው ሄደ ሰው መጣ ሄደ ጉዳዬ አይደለም ነው የዚህ ግጥም እሳቤ፡፡

የቀድሞ ባሏ መበለጡ አንገብግቦት ይመስላል፤ ከመሞከሻሸት ከመበሻሸቅ የፍቅር ግጥም ወጥቶ ለጥቂት ደቂቃዎች አብሰልስሎ የሚከተለውን ግጥም አስቀመጠ

ደገኛ ሱሪውን ይለዋል ወንጨሬ

እኔስ እኖራለሁ እንዳባቴ ጭሬ

ግጥሙ የቁጭት ነው፤ ‹እሱ ቢቀርብኝ በራሱ ውስልትና ነው› መባሉ አንገብግቦት ይመስላል፤ ለዚያም ነው እኔኮ እንደአባቶቸ አርሽ የምበላ ሀገር ያወቀኝ ጸሐይ የሞቀኝ የኮራሁ ገበሬ ነኝ ለማለት የዳዳው፡፡ እሷ ለማተባ ስትሞት እኔ የትም እንደተገኘ፣ ሃይማኖቱ ማንነቱ እንደማይታወቅ እንዴት በእኔ ላይ ትዘባበትብኛች ነው የሰውየው ግጥም፡፡ ነገር ግን የፈታችው ሚስቱ ቀላል አልነበረችም በደቂቃዎች ውስጥ ሌላ ግጥም አውርዳ ቀንድ አስበቀለችው!

መሬቱ አርባ ክንድ በሬው የተውሶ

እንጀራው ሊበላ እንዲህ ሆኖ ታርሶ

ማተብ ማክበሩ ላይ ችግር አለብህ መባልህ ምን አንገበገበህ ነው የዚህ ግጥም ነጥብ፤ ይባስህና እርሻስ የት ታውቅና! ነው የዚህ ግጥም ነጥቡ፤ በዚያች መሬት ላይ በተውሶ በሬ አርሰህ እንዴት ታኖራታለህ? ታታሪ ብትሆንማ እንዲህም እንዲያም ያለውን ስራ ትሰራ ነበር፤ ሌላው ቀርቶ አርሶ ለመብላት እንኳ ያልበቃህ አንተ እንዴት ነው እንደገበሬዎቹ ገበሬ ነኝ ብለህ የምትኩራራው ነው የግጥሙ መሰረት፡፡

የሴትዮዋ ግጥም የታለመለትን ግብ መምታቱን ለማወቅ ባሏ ሞቶባት ከዚህ ሰው ጋር ሌላ የፍቅር ግንኙነት የመሰረተችው ሴት ያመጣቸውን ግጥም እንመለከት፡፡

የእናት ያባት እዳ የለብኝ ብድር

ምነው ለምቀኛ እንባ ምሰፍር

ይሄ ግጥም ስሜት እንጅ እውነት ያለው አይመስልም፡፡ ሴትዮዋ የምትለው ኑሮዬ መራራ የሆነው በምቀኞች የተነሳ ነው፣ ምቀኞች እየተከታተሉ መግቢያ መውጫ ያሳጡኛል፣ ይህችም ሴት የፈታችውን በሷን ብወሽም ምቀኛ ሆነችብኝ ነው፡፡ የሴትዮዋ መከራከሪያ፡፡ ሁነቱ ግን ከግጥም ወጥቶ ደርዝ ወዳለው ምክክር ተሻገረ፡፡ የሚገሰጻውን ለመገሰጽ፡፡

በዚህም ምግባር ላይ ባተኮሩ የስለምን ግጥሞች ለማረጋገጥ እንደተቻለው የአካባቢው ማህበረሰብ ሰው ምን ይለኛልን የሚፈራ መሆኑን ነው፡፡ የአካባቢው ሰው ‹‹ሰው ምን ይለኛል›› ብሎ በመፍራትም ማኅበረሰቡ የሚጠብቅበትን እና ልክ ነው የሚለውን ሁሉ እንደሚሰራ ነው፡፡

ከሚስቱ ተፋትቶ ባሏ የሞተባትን ሴት በፍቅር መቅረብ በዚያ ማህበረሰብ ዘንድ ነውር ነው፤ ነውርነቱ የፈታት ሚስቱም ብትሆን እዚያው ማህበር ውስጥ ያለች መሆኑ እሷን ለማበሳጨት መምሰሉ፣ ወዲያውም ከዚህ በፊት ባለእንጀራው የነበረውን ሰው ሚስት በፍቅር መፈለግ ከወንድም ሚስት ጋር እንደመተኛት ያለ ነውር ተደርጎ በማኅበሰረቡ መወሰዱ ነው፡፡ ይሄን ሁሉ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ ተቋም አቅርበው አልተከራከሩም፣ ይልቁም ራሳቸው በፈጠሯቸው ግጥሞች ተወራረፉ፣ ተፎካከሩ፣ በስተመጨረሻም አጀንዳ ሆነው ለምክርና ለግሳጼ ክፍት ሆኑ፡፡

## ሐ.ኢኮኖሚ ላይ ያተኮሩ ግጥሞች

እነዚህም ግጥሞች የተሰበሰቡት የማርያም እለት ነው፡፡ ዋናው ድግስ በመሆኑ ሰፊ ነጻነት ይሰጣልና፤ በአካባቢው ልማድ በማርያም ቀን ስራ ስለማይሰራ ለረጅም ጊዜ የድግሱ ዳስ ውስጥ ለመቀመጥም እድል ስለሰጠ ሊሆን ይችላል የእለቱ የግጥም ጎርፍ ትንሽ አልነበረም፡፡ ኢኮኖሚ ላይ የመጡት ግጥሞች የተጀመሩት አንድ ግጥም አውቃለሁ ባይ በሰራው ስህተት ነበር፡፡ የጠጣው ለስህተት አነሳስቶት ወይም አጉል ድፍረት ሰጥት ባይታወቅም እንደጨዋታ አዋቂ ይታይ ይመስል ይሄንን ግጥም ሰነዘረ፡፡

ሸማኔ ሲበላ የለውም ትንፋሽ

ቀና ብዬ ባዬው ባዶ ቀለምሻሽ

የሚል ግጥም ተናገረ፤ (ይህ ወርቀት አቅራቢ ቆይቶ እንደተረዳው ይሄ ግጥም የቆየና ማኅበረሰባዊ ግጥም ነው፤ ሰውየው በዚያ ሰዓት ግጥሙን ያለው አንድ የተቀየመውን ሰው ለማስቀየም ብቻ ነበር)፡፡ የመሬት ጥበትና የከተሜነት መስፋፋት ከመጣ ወዲህ ሰዎችን በቀለማቸው ወይም በስራቸው ማግለሉ እየጠፋ መጥቷል፡፡ አብችክሊ ዙሪያም የዚህ ጠበል ቀማሽ በመሆኑ በ2010 ሸማኔ በስራው የሚገለልበት ወቅት አልነበረም፡፡ ስለሆነም ግጥሙን ያቀረበው ሰው የተቃውሞ ምላሽ ሲያገኝ ብዙ አልቆየም

ወርደህ ጥመድ እንጅ ማን ይረስልህ

ቦላሌ አውልቀህ ቁምጣህን ለብሰህ

ይሄን ግጥም የገጠመው በቀበሌው የሚታወቅ ገበሬ ነው፡፡ በጋ በጋውን የጓሮ አትክልት ያመርታል፡፡ በመኸር በርትቶ ያርሳል፡፡ የወረቀቱ አቅራቢ እንዳጣራው ገበሬው ‹እጁን እግር› አድርጎ የሚሰራ ታታሪ ነው፡፡ የሆነው ሆኖ በግጥሙ ሊል የፈለገው ስራ መስራት ክቡር ነው፤ ያልሰራ አይበላም የሚለውን ሲሆን ‹ቦላሌ አውልቀህ ቁምጣህን ለብሰህ› የሚለው ሀረግ የመጀመሪያውን ግጥም ተናጋሪ ቃል በቃል ለመቃወም የገባ ይመስላል፡፡

የመጀመሪያው ግጥም ተናጋሪ ባቅራቢያው ወዳለችው የወረዳ ከተማ ነጋ ጠባ መመላለስን

እንደከተሜነት የሚቆጥር፣ ከማረስ ይልቅ በዚህና በዚያ ስብሰባዎች ላይ መገኘትን የሚመርጥ አጠር ሲል ‹ዘመናዊ› ነኝ የሚል ነው።

በአካባቢዋ ሙሉ ሱሪ ወይም ቦላሌ መልበስ የዋልጌነት እንጅ የከተሜነት መገለጫ አይደለም፤ በስራ ቀን ቦላሌ ለብሶ የሚታይ ሰው ‹‹ስራ ፈት›› ነው፤ ስራ የማይወድ ነው፣ አውደልዳይ ነው፤ ይልቁንም አጠር ያለ ቁምጣ ለብሶ ‹‹ከአፈር ጋር አፈር መስሎ›› ሲሰራ የሚውል ሰው ይሞገሳል። ያም ገበሬ ለዚህ ‹ገልቱ› ሰው በግጥሙ የነገረው ይሄንኑ ነው።

ይመጠጣል እንጅ አይበላም ሎሚ

ለመለኪያ አረቂ ምትስለመለሚ

ይሄኛውን ግጥም የገጠመችው ደግሞ ሴት ናት። የወረቀቱ አቅራቢ ገጣሚዋ ምን ለማለት እንዳሰበች ለመረዳት ጊዜ እና ረዳት አስፈልጎታል። ነገር ግን በዚያ የነበሩ ሰዎች ግጥሙን ሲፈታቱት አስቀድሞ በሽማኔ ስራ የዘበተውን ሰው ማንነት መሰረት አድርገው ነው።

ሰውየው ከተማ የሚመላለሰው አረቂ ፍለጋ ነው። የአረቂ መለኪያ ከጨበጠ ‹‹እንኳንስ ለስራ ሊነሳ ዘመድ ሞቷል ቀበር›› ቢባል እንኳ ላለመነሳት የሚያቅማማ ነው። ከዚህ ሰው አንድ ነገር የፈለገ ሰው ጥቂት መለኪያ አረቂ መጋበዝ ብቻ ይጠበቅበታል፤ ከዚያ እየተስለመለመ ሰው የፈለገውን ያደርጋል። እናም ይህች ሴት ‹‹አንተ ማን ሆነህ ሰውን ልትተች በቃህ›› ስትል በዚህ ግጥም ወረፈችው።

ገበሬ መሆኔን እኔ እወደዋለሁ

እሸቱን ከጓሮ ቆርጨበታለሁ

ይሄኛው ግጥም አዲስ አይመስልም፣ ነገር ግን በስፍራው አንድ ሽበቶ ሰውየ ያሉት ነው። እኒህ ሰውዬ ግጥሙን ተናግረው ብቻ አልቆሙም ይልቁንም የግጥሙን ሐሳብ እንደሚከተለው አብራሩ።

> ሰው ከእንስሳ የሚለየው ያለፈውን በትዝታ የሚመጣውን በተስፋ ስለሚኖር ነው። ሰው ተስፋና ትዝታ የሚኖረው ደግሞ እግዚሀር በሰጠው አቅም ሲሰራ ውሎ ሲገባ ነው፡፤ ሰርቶ የበላ ሰው ምግቡ ይጥመዋል፤ መጠጡ ያረካዋል፤ ሲነጋ ደስ ይለዋል፤ ስራ የማይወድ ሰው በበጋ ሰው ይመስላል፤ በክረምት የሚልሰው የሚቀምሰው አጥቶ የሰው ደጅ ላይ ይወድቃል፤ የሚሰራ ሰው ግን በክፉ ቀን እንኳ እሸት (ጨገዳ) አያጣም። አዲያ ሰው እንደሙያው፣ እንደጁ ቢሰራ ይሞገሳል እንጅ ይወቀሳል ወይ? የሚወቀስስ ገልቱ፣ ሴት አውል፣ ከተማ አውደልዳይ እጁ ልስልስ የሆነ ሰው ነው።

በእነዚህ ጥቂት ግጥሞች መስራት እንደሚያስከብር፤ እንደሚያኮራ፣ ባንጻሩ መለመን ጸያፍ እንደሆነ የአካባቢዋ ነዋሪዎች እንደሚያምኑ ለማዬት ይቻላል። ልመናን መጸየፍ ስራን መውደድ ደግሞ ለአንድ ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ጥንካሬ መሆኑ ማብራሪያ የማይጠይቅ ሀቅ ነው። ቃል ግጥም ማኅበረሰቡ የጋራ በሚላቸው አደባባዮች ክብርን የሚያገኝ፣ የሚወደድ ወይም የተመሰገነ ሰው ሆኖ ለመገኘት የሚያስችሉ ጥበቦች በምክር መልኩ የሚለገሱበት ዘዴ መሆኑንም በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል።

## ማጠቃለያ

በደቡብ አቸፈር ወረዳ አብችክሊ ዙሪያ አካባቢ የተሰበሰቡት የስለምንቃል ግጥሞች ማኅበሰረቡ በራሱ አመቻችነት፣ በራሱ ዳኝነት፣ በራሱ ተሳታፊት አጥፊዎችን የሚወቅስበት፣ ብርቱዎችን የሚያሞግስበት፣ ክፉውን የሚያመላክትበት፣ ደግ ደግኑን የሚያሞግስበት ማህበራዊ የሂስ መድረክ ነው። ከዚህ ማኅበበረሰባዊ ሥነቃላዊ ሀብት የምናገኛቸው ቁም ነገሮች እንደሚከተለው ጠቅለል ሊደረጉ ይችላሉ።

1. ማንኛውም የማኅበሰረቡ አባል በጾታ በእድሜ በሀብት ወይም በሌላ መስፈርት ሳይበጅለት ሁሉም በእኩልነት የሚሳተፍበት ነው።

2. ማኅበረሰባዊ ጠንቆችን ነጥሎ ማውጣትና አካላዊ ቅጣትን በመቅጣት ሳይሆን በማሳፈር በማሸማቀቅ ለማኅበሰረቡ ጠንቅ የሚሆኑ ምግባር ያለባቸውን ግለሰቦች ማረቂያ መንገድ ነው።

3. ማኅበሰረቡ ማንነቱን እንዳይረሳ በሰው ላይ ክፉ እንዳያደርግ ተንኮለኛ እንዳይሆን ሁነኛ የማኅበራዊ ቁጥጥር ዘዴ ሆኖ ያገለግላል።

4. ዘመናዊው አኗኗር የማይመልሳቸው ወይም በተቃራኒው የሚጠፍ ማህበራዊነትና የማህበራዊነት መገለጫዎች እንዲጎለብቱ ኅብረተሰቡ ግላዊ በሆኑ አመለካከቶች እንዳይበረዝ ሚዛን መጠበቂያ ሆኖ ያገለግላል።

5. አዳዲስ መረጃዎችን ለማስተላለፍና ነባር ታሪክችን ለማቆየት የትርክት መድረክ በመሆን ያለግላል።

## ማጣቀሻዎች

Bourricaud, F. (1976). *The Sociology of Talcott Parsons*. Chicago: Chicago University Press.

Cassell, P. (1993).*The Giddens Reade.* The Macmillan Press Ltd, pp. 6

Fish, J. S. (2005). *Defending the Durkheimian Tradition. Religion, Emotion and Morality*. Aldershot: Ashgate Publishing.

Cuddon J. A. (2013). *A dictionary of literary terms and literary theory*,5th ed. London: Blackwell Publishing.

Finnegan, R. (1977). *Oral Poetry Its nature, significance and social context,* Wipf and Stock Publishers.

Finnegan, R. (1970). *Oral Literature in Africa.* Oxford: Oxford University Press.

Giddens, A. (2005).*The Constitution of Society in The Giddens Reader*, Philip Cassell (eds.) MacMillan Press.

Merton, R.K. (1957). *Social Theory and Social Structure*, Revised edtion, Glencone.

Parsons, T. (2005). *The Present Status of "Structural-Functional Theory in Sociology*

Parsons, T. (1975). *Social Systems and The Evolution of Action Theory*. New York: The Free Press.

Urry, J. (2000). ‘’Metaphors’’ (http:// books. google. co. uk/ books? id=ogyDBobOHVEC& pg=PA23). Sociology beyond societies: mobilities for the twenty-first century. Routledge. p. 23. ISBN 978-0-415-19089-3.